# ቴዲና የፍቅር ሥራዎቹ

ከእንቆጳ (inkopa@yahoo.com)

«ፍቅር አጥተን እንጂ በራብ የተቀጣን
አፈሩ ገራገር ምድሩ መቸ አሳጣን »

የቴዲን ዜማዎች ስንስማ ቃላቶቹን እናስተውላቸዋለን? ወይስ ከውስጡ መርጠን ለኛ የሚስማማንን ብቻ ነው የምንሰማው? ለምሳሌ፡-

«ባስራ ሰባት መርፌ በጠቀመው ቁምጣ
ለለውጥ ያጎፈረው ስልጣን ላይ ሲወጣ . . . » የሚለውን

ይህንን የምለው ካጋጠመኝና ከምሰማው በመነሳት ነው፡፡ እሰኪ ነገሬን አንድ ሁለት ብዬ ላስቀምጥ፡፡ ቴዲን መጀመሪያ ስሰማው ከላይ የጠቀሰኳትን ስንኝ ሰምተው በተደመሙ አድማጮቹ ተጋብዤ ነበር፡፡ እኔም ትንሽ ነገሩ ገርሞኝ አዳመጥኩት ፣ አጠቃላይ ይዘቱን ግን ታላቅ መልእክትን የያዘ ሆኖ አግኘሁት፡፡ እንዲህ የሚደመጠውን፡-

«ግርማዊነታቸው ከዚህ ሰረገላ
ወደ ዋገን ወርደው ሲተኩ በሌላ
ባዛውንቶች እራስ ስድሳ ጉድጓድ ምሳ
አብዮት ሞላችው የተማሪን ሬሳ፡፡
ባስራሰባት መርፌ በጠቀመው ቁምጣ
ለለውጥ ያጎፈረው ስልጣን ላይ ሲወጣ
እንዳምናው ባለቀን ያምናውን ከቀጣ
አዲስ ንጉሥ እንጂ ለውጥ መቼ መጣ፡፡»

ይህ እንግዲህ እኔን እስከገባኝ ድረስ የኛ የኢትዮጵያውያን የትናንት እና የዛሬው ታሪካችን ነው፡፡ የ ከትናንት በስቲያውን ባለወርቅ ቅቡን የአያቶቻችንን ታሪክ አያካትትም፡፡ ይህንን ያልኩት ብዙዎች «ጃ» በሚለው ተቀጥላ ብቻ ዋናውን መልእክት ሊዘሉት ሲቃጡ ስለማስተውል ነው፡፡ ያለፉት ሁለት አገዛዞች አጨራረስ ለአሁኑ ምስቅልቅል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በር ከፍቷል፡፡ ከዘውዳዊው አገዛዝ የቀጠሉት ሁለት ገዢዎች መንደርደሪያቸው «ለውጥ» ነበር፡፡ የቀደመው «ያለምንም ደም . . . » በማለት የ«ለውጥ» ሐዋሪያነቱን ነጋሪት ሲጎስም ፤ ሁለተኛው ደግሞ «በቀን ሶስት ጊዜ» ሊመግበን ፤ «ጠብመንጃን ወደ ማረሻ ሊለውጥ» እና «የዴሞክራሲ ፋና ወጊ» ሊያደርገን ነበር፡፡ ቴዲ እንደሚለው ግን ሁለቱም የጎደላቸው ነገር ነበር፡፡ ይኸውም «መወቃቀስ» ብሎም «ይቅር መባባል» አያውቁም፡፡ አንዱ ለውጥ ማምጣት

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የሚፈልገው ሌላውን አጥፍቶ ነው እንጂ ወቅሶና መክሮ አይደለም። ውጤቱንም እንደምናየው ነው። የቴዲ መልዕክት ታዲያ ይህንኑ የታሪክ አዙሪት እና መዘዙን ካስረዳን በኋላ አሁንም እየተሳሳቱ ያሉትን እንዲህ በማለት ይመክራል፡

«ይቅር በለው እና የበደለን ወቅሰህ
ምህረት አስተምረን አንድ አርገን መልሰህ . . .
በተስፋዋ ምድር እንዲፈፀም ቃሉ
ሞፈሩን ያዙና ይቅር ተባባሉ»

እንደዚህ እያለ ያለፉ ስህተቶቻችንን በመጠቆም ለወደፊቱ ምን ብናደረግ አሸናፊዎች እንደምንሆን ያሳስበናል። የቴዲ ስራዎችን ዘመናዊ የሚያሰኛቸው የሙዚቃ ስልታቸው ብቻ ሳይሆን ቃላቶቹም ናቸው። እንደኔ አስተያየት አርቲስቶች ከህዝብ አብራክ ስለሚወጡ ስራዎቻቸውም ህዝብን ይወክላሉ ብዬ አምናለሁ። ከዚህ አንጻር እንግዲህ ለአንባቢዎቼ ጥያቄ ለማቅረብ እገደዳለሁ፡- የቴዲ መልእክቶች በርግጥ ይወክሉናል? ቃላቶቹ የክፋት ሰራዊቶችን ጆሮ ኮርኩረዋል። እንቅልፍ አጥተው ሴራ ጠንስሰው (ያውም በደንብ ያልተጠናና መላው የጠፋ ሴራ) ወደጨለማ ሲወረውሩት «ለምን?» ብለን ማንንም ሳይሆን እራሳችንን ጠይቀናል? ቴዲ የትኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ ሳይወክልና ምንም ትጥቅ ሳያነግብ ፍቅርን ፣ ሰላምንና እርቅን ፣ መተሳሰብን እና ወንድማማችነትን ብቻ እየሰበከ እዚህ ደርሶአል። ወደፊትም የሚያቆመው ሃይል አለ ብዬ አላምንም። «ጨለማ ብርሀንን ሊያጠፋ  ከቶ አይቻለውምና»! ደግሞስ ብርሃን ጎልቶ የሚታየው በጨለማም አይደል? እኛስ? ሳናውቀው በጨለማ ያሉት ላይ ጣት ስንጠቁም እዚያው ተቀላቅለን ከሆነስ? ብርሃን አያስፈልገንም? የቴዲ መልእክቶች ለጥፋት ሰራዊቶች ገብቷቸው «መፍትሄ» የሚሉትን ተግባራዊ ሲያደረጉ እኛስ ዜማዎቹ በጆሮዎቻችን ተንቆርቁረው ህይወት ዘርተው ለውጠውናል? ወይስ በጭፈራና በእስክስታ አባዜ ከጆሮዎቻችንን ጋር ተላልፈው በአየር ውሰጥ ሰጥመው ቀርተዋል?

የቴዲ ሙዚቃ ባለፉት 17 ዓመታት ከምኒልክ ቤተመንግሥት በቀጥታ ለህዝባችን ከሚተላለፈው ሌላ ሙዚቃ ጋር አለመስማማትን ፈጠረ። የገዥው ፓርቲ ሙዚቃም ሁለተኛ ላይስተከከል ተበላሸ። የቴዲ ሙዚቃ በአገራችን ሞገድ ላይ ተሰራጭቶ ህዝባችንን ሲመርዝ ለነበረው የጥላቻ ፣ የቂም በቀል ፣ የመከፋፈል ፣ የመወነጃጀል ወዘተ አስተሳሰብ ማርከሻው ሆነ። ለክፋት ደግነትን ፣ ለጥላቻ ፍቅርን ፣ ለበቀል ይቅርታን ፣ ለመከፋፈል አንድነትን ፣ ለመበጣበጥ ሰላምን ይዞ ብቅ አለ። ልብ ብለን ካስተዋልነው ከዚህ የበለጠ ትግል የለም!

በአገራችን አሁን ያለው ጠላት የአስተሳሰብ ነው። እርሱም ያለው ከእያንዳንዳችን ጉያ ነው። ሁላችንም ራሳችንን ብንመረምር ጠላት ፍለጋ ሩቅ መሄድ አያስፈልገንም። ከኛው እንጀምር እና ያንን ልምድ ይዘን ወደውጭ እንውጣ። ጦርነቱን ከራሳችን ጀምረን በራሳችንን አስተሳሰብ ላይ ድልን ብንቀዳጅ ሌሎችን እንማርካለን። የጥፋት መልእክተኞች ለ 17 ዓመታት ሲያጋቡብን ከከረሙት የቂም ፣ የጥላቻና የመከፋፈል ህመም ከዳንን ሌሎችንም ለመፈወስ እንችላለን። ከዚያም በህብረት ፣ በፍቅር እና በመተሳሰብ ለጋራ ብልፅግና ብንሰራ «ጠላታችን» (ልብ በሉ ሰው አይደለም) በቀላሉ ድል

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ይነሳል፡፡ ምክንያቱም የሚጋልበው ፈረስ ፤ የሚቀመጥበት ዙፋን አይኖረውም፡፡ በአጭሩ እኛ ላይ ሊቀመጥ የሚችለው በውዴታ ስናነግሰው ነው፡፡ የማያስፈልገንን ወይም የማይመጥነን አሰተሳሰብ የምናጠፋው እኛ ሳንሆን እራሱ ስለማይመቸው ብቻ ይሆናል፡፡

ባለፉት ምእተ ዓመታት ኢትዮጵያዊነት ፈተና ላይ ያልወደቀበት ጊዜ አልነበረም፡፡ የኢትዮጵያዊነት ጠላቶች ተራ በተራ እየመጡ ታግለው ተሸንፈዋል፡፡ አሁን ግን እነሱ አልመጡም የላኩት ድምጻቸውን ነው ፤ የላኩት ሀሳባቸውን እና መንፈሳቸውን ነው፡፡ እኛ ደግሞ ይህንን የምናሸንፍበት ሌላ መንፈስ አለን፡፡ «ቅንጅት መንፈስ ነው!» እንደተባለው ሁሉ ኢትዮጵያዊነትም መንፈስ ነው፡፡ የተዠጎረጎረ መንፈስ ፤ ጉራማይሌ መንፈስ ፤ የተለያየ የሚመስል ግን የተገመደና የማይበጠስ መንፈስ፡፡ የሱማሌ ፣ የቆቱ ፣ ያደሬ ፣ የወላይታ ፣ የከንባታ ፣ የቤንሻንጉል ፣ የቅማንት ፣ የሸናሻ ፣ የሞቻ ፣ የመዠንገር ፣ የአኝዋክ ፣ የኑዌር ፣ የትግሬ ፣ የኦሮሞ ፣ የጉራጌና . . . መንፈስ፡፡ ይህም መንፈስ ዛሬም እንደትናንቱ ሊሸነፍ አልቻለም፡፡ ለዚህም ማስረጃው ከዚያው ከኢትዮጵያዊነት መንፈስ የተወለደው ቴዲና እሱን የመሳሰሉ ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡ ከኋዋላቸው ደግሞ ብዙዎች ተሰልፈዋል - የአንድነትን ፣ የፍቅርን እና የሰላምን መዝሙር የሚዘምሩ፡፡ ከእነርሱ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘን እንትመም፡፡

አንድ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ያሉትን በመጥቀስ ነገሬን ልቋጭ «ኢትዮጵያዊነት አሻፈረኝና እንቢ ባይነት ነው»፡፡ አዎ እንቢ ለጎጠኝነት ፣ እንቢ ለጥላቻ ፣ እንቢ ለጸረ ኢትዮጵያዊነት፡፡

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com